በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS

ፕሬስ መግለጫ PRESSRELASE

# የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ የሀገራችን የውጭ ግንኙነት ዋነኛ ትኩረት ሆኖ ይቀጥላል

የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ የሀገራችን የውጭ ግንኙነት ዋነኛ ትኩረት ሆኖ እንደሚቀጥል እና ኢትዮጵያ ለአካባቢዋ አበክራ እንደምትሰራ ጠቅላይ ሚኒሰትር ኃይለማሪያም ገለፁ፡፡

አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ከሚስዮን መሪዎች እና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራር ጋር ዛሬ ባደረጉት ውይይት ዲፕሎማቶች በሁለተኛው እድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በተቀመጠው መሰረት በተመረጡ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንቶች ላይ ትኩረት በማድረግ ባለሃብቶችን ለማፈላለግና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማሳለጥ የተጠናከረ እቅስቃሴ ማድረግ አለባቸው ብለዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት የማስፈፀም አቅሙን መገንባት እንደሚኖርበት እና በበቂ ጥናት ላይ የተመሰረተ ስትራቴጂያዊ እንቅስቃሴ ማድረግ እንዳለበትም ጠ/ሚ አሳስበዋል፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ከሌሎች ከፍተኛ እና የምርምር ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ መስራት አለበት ያሉት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሀገሪቷን ግንኙነት የውጭ እቅስቃሴ በተመለከተ ምሁራን፣ ነጋዴዎች፣ ባለሀብቶች በአጠቃለይ ህብረተሰቡ በቂ መረጃ እንዲኖራቸው የኮሚኒኬሽን እና የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስራ መስራት አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ሰላም እና መረጋጋት እንዲሰፍን በኢጋድ ጥላ ስር የምታደርገውን ጥረት አጠናክራ እንደምትቀጥልም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልፀዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚስዮን መሪዎች እና የመስሪያ ቤቱ የበላይ አመራር ነሀሴ 25 እና 27 በአዲስ አበባ እንዲሁም ከነሀሴ 28 አስከ ጳጉሜ 3/2009 ዓ.ም በሃዋሳ ከተማ በባለፈው በጀት ዓመት በተከናወኑ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎች እና በዚህ ዓመት መከናወን በሚገባቸው አንኳር ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት መካሄዱ ይታወሳል፡፡

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**

**መስከረም 2 ቀን 2010 ዓ.ም.**

E-mail spokesperson@mfa.gov.et facebook @mfaEthspokesperson, Twitter @mfaEthspokesperson,
YouTube https://www.youtube.com/channel/UCa_KUDpwCLMWyyQIjfilgZg ☎ 011-5-15 8928/011-5-53 6731 Fax 011-5-51-43-00
✉393 Addis Ababa,Ethiopia